**ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 18 ቀን 2008 ዓ. ም.)**

**ቴዲ አፍሮ ለሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጠረ፣ የቴዲ አፍሮ ቲሸርት እንዳይሸጥ ፌዴራል ፖሊስ ከለከለ፣ ወያኔ በርካታ ሰዎችን አፍሶ ለእስር ደረገ ግማሹ የደረሰበት አልታወቀም፣ ሠራተኛው ከስራ ሊባረር እቅድ መኖሩ ተጋለጠ፣ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ የወያኔ ፖሊሶች ማዕረግ ሊሰጣቸው አሌልቱ ገቡ፣ ወያኔ በራሱ ሚኒስትሮች ላይ ሹም ሽር አደረገ፣ የአፋር ክልል ፀጥታው አስጊ በመሆኑ የፌዴራል ፖሊስ መዝመቱ ተጋለጠ፣ የተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ሠራተኞች አፈ ጉባኤ ተሾመ ቶጋን አሳፍረው መለሱት** »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ በዝርዝር ለማበብ እዚህ ይጫኑ .....**

******************************************************************************************

**እውቁ ኢትዮጵያዊ ዘፋኝ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ረቡዕ ሚያዝያ 8 ቀን 200. ዓ.ም «ሰው ገድለሃል» በሚል በወያኔ ሴራ በሀሰተኛ ክስ ተመስርቶበት ወደ ወህኒ መውረዱ ታወቀ::**

**ክሱ በጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል አካባቢ የጐዳና ተዳዳሪ በመኪና ተገጭቶ ሞቶ ተገኘ ተብሎ ሲሆን፣ በዕለቱ ቴዲ ከብዙ ወራቶች ቆይታ በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ የገባበት ዕለት ከመሆኑ ጋር ተገጣጥሞ አደጋውን አድርሰሃል ተብሎ በተቀነባበረ የሀሰተኛ የፈጠራ ክስ ተከስሶ፣ ትራፊክ ፖሊስም አጣርቶና እንዳልፈፀመው አረጋግጦ ለቆት ነበር:: ቢሆንም ወያኔ እስከወዲያኛውም ድረስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሊገናኝ በማይችልበት ወቅት ላይ ደርሶ የቁርጥ ቀን ልጁን ቴዲን ከአብራኩ ወስዶ ለእስር የዳረገው በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በብስጭትና በንዴት እየበገነ መሆኑ ታውቋል::**

**ባልፈፀመውና ባላደረገው ለዚያውም ፖሊስ እንዳልፈፀመው ካረጋገጠ በኋላ ከአንድ ዓመት ከ6 ወር በላይ ቆይተው ወያኔዎች እንደ አዲስ ክስ መስርተው የእውቁን ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ሞራል ለመንካትና በሕዝብ ዘንድ ያለውን ተወዳጅነት ለማሳሳት ያደረጉት ሙከራ ቢሆንም ሕዝብ ከወትሮው በተለየ ያለውን አድናቆት እየሰጠው መገኘቱ ለወያኔ ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነባቸው ለማወቅ ተችሏል::**

**የቴዲ አፍሮ ክስ በአዲሱ ሕግ ከ5 ዓመት እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጣ አንቀፅ ከፍተውበት ከቀረበበት በኋላ የዋስትና መብት እንደማያሰጥ ተናግረው ይህንኑ ጉዳይ ለማየት ለሰኞ ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥተው ወደ ወህኒ ያወረዱት ሲሆን፣ ሰኞ ፍ/ቤት ቀርቦ ከሁለት ቀን በኋላ ሚያዝያ 15 ቀን 2000 ዓ.ም በድጋሚ ቀርቦ ለሚያዚያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ መስጠታቸው ታውቋል::**

***የሚያዝያ 13 ቀን ውሎ***

***እውቁ ኢትዮጵያዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) 3:00 ሰዓት ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 8ኛ ችሎት የቀረበ ሲሆን፣ ዳኛው ከ30 ደቂቃ በኋላ ቀርቦ ፋይሉን ካየ በኋላ አቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶት ለሚያዝያ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጥሮት ነበር፡፡***

ሰኞ አለት ለመጀመሪያ ጊዜ የከፍተኛው ፍ/ቤት ግቢ በሕዝብ ብዛት ተሞልቶ መንቀሳቀሻ ጠፍቶ የነበረ ሲሆን ወደ ፍ/ቤት የሚገባ ባለጉዳይም ሆነ ማንም ሰው እንዳይገባ በፌዴራል ፖሊስ ተከልክሎ እንደነበር ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አማኝነቱን ሰጥቷል፡፡

በተለይም ከፍ/ቤት ግቢ ውጭ አንድ ዙር ከውስጥ ሌላ ዙር በፌዴራል ፖሊስ ተከብቦ የነበረ ሲሆን፣ ሲቪል የለበሱ ፖሊሶችና ደህንነቶች ከሕዝቡ በማይተናነስ ቁጥር ታጭቀው የነበረ መሆኑን ያረጋገጠው ዘጋቢያችን ቴዲ አፍሮ ቀጠሮ ተሰጥቶት ሲወጣ ሕዝቡ «ቁርጠኛ ኢትዮጵያዊው ይፈታ፣ በፈጠራ ክስ አይታሰርም፣ እውነት ትቀጥናለች እንጂ አትበጠስም. . . » የሚሉና ሌሎችም መፈክሮች፣ በከፍተኛ ድምፅ ግቢውን ሲያናውጡት እንደነበር ከተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

በወቅቱ ሌላ ተደብቀው የነበሩ ነጭ ቆብ የደፉ የፌዴራል ፖሊሶች አስለቃሽ የጭስ ቦምብ ታጥቀው መፈክር ወደሚያሙት እየተጠጉ ለማስፈራራት ሙከራ ያደረጉ ሲሆን በሁለቱም ቡድን መካከል እየከረረ የመጣው ግብግብ አላስደስት ያላቸው ፖሊሶች ቴዲ አፍሮን በሽፍን መኪና 4 ሰዓት ላይ በጓሮ በር ደብቀው በመውሰዳቸው ግብግቡ ሊበርድ እንደቻለ አስረድቷል፡፡

ወያኔ እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን በሚያቀርባቸው ሙዚቃዎች እየበገነ ሲሆን፣ አጋጣሚውን አግኝቶ ለማንገላታት እና በሞራሉም ላይ ለመጫወት ከሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ቃሊቲ እስር ቤት በጠያቂዎች የተጨናነቀ ሲሆን፣ በተለይም ቅዳሜና እሁድ ፖሊሶች እንኩዋን ለማስተናገድ ተቸግረው በሺዎች የሚቆጠሩ አድናቂዎች አጨናንቀውት ስለነበር ልዩ ኃይል ተመድቦ እንደነበረም ለማየት ተችሏል፡፡

ቴዲ አፍሮ በሚያወጣቸው በሳል ግጥሞቹና ለሀገሩና ለሕዝቡ ያለውን ፍቅርና ክብር በመግለፁ ብቻ የወያኔው ቡድን እሬት ሆኖባቸው አልዋጥ ብሏቸው የነበረና አሁንም በጥላቻ የሚመለከቱት ሲሆን፣ በተፈጠረላቸው አጋጣሚ ተጠቅመው በሀሰተኛ የፈጠራ ክስ ሊያጥላሉት መሞከራቸው በእጅጉ የዕውቀት ድውዮች መሆናቸውን የገለፁት አንድ የሕግ ባለሙያ ቴዲ አፍሮ ብቻውን ከወያኔው በድን በላይ ታዋቂ እና እጅግ አድናቂ ያለው በመሆኑ አምነው መቀበል ያቃታቸው የእውቀት ድሃዎች መሆናቸውን ያረጋገጠ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ዛሬ ቴዲ አፈሮን በሀሰተኛ ክስ የሚያንገላቱት ባላቸው ጥላቻ የተነሳ ሲሆን፣ አሁንም በቀጠሮ የሚያመላልሱት ምን ያህል ደጋፊ አለው ብለው ለመገምገም የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ በፖሊስ ኃይል ተገድቦም ቢሆን እያጨናነቀው መሆኑን ሲመለከቱ በድንጋጤ መዋጣቸው ተስተውሏል ብለዋል::

ቴዲ አፍሮ በወህኒ ቤት ውስጥ እንደገባ ዞን 6 ተብሎ በሚታወቀው በሌብነት ተይዘው ከታሰሩት መካከል እንዲቀላቀል ያደረጉት ሲሆን፣ በዚያን ወቅት ዞን 3 የሚባለው ውስጥ ያሉት እስረኞች «አበባዬ ሆይ » በማለት ለቴዲ ከፍተኛ አቀባበል ያደረጉለት ከመሆኑም በላይ «ቴዲ አፍሮ የቁርጥ ቀን ልጅ» እያሉ በማሞገሳቸው የተበሳጩት የእስር ቤቱ አዛዦች አመፅ ለማነሳሳት የሞከራችሁ እናንተ ናችሁ በማለት 25 ወጣት እስረኞችን መርጠው አውጥተው ጨለማ ቤት ተብሎ በሚታወቀው አየር እንኩዋን በማይገኝበት ቤት ማጉራቸው ታውቋል::

ረቡዕ ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ቴዲ ዞን 6 በአደገኛ ቦዘኔነት የታሰሩት መሀከል ያስገቡት እንዲያስቸግሩትና ጉዳት እንዲያደርሱበት ሆን ብለው ያደረጉት ቢሆንም እስረኞቹ ግን ለቴዲ ልዩ አቀባበል በማድረጋቸው እጅግ የተበሳጩት የወያኔ ሹማምንቶች በማግስቱ ሀሙስ ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም አዛውንቶች የሚታሰሩበት ዞን 5 ውስጥ ማዛወራቸው ታውቋል::

ዘመድ ለመጠየቅም ሲመጣ እንደማንኛውም አስረኛ በመጠየቂያና ስንቅ በማቀበያው በኩል ሳይሆን በአስተዳደሩ ቢሮ በኩል ጠያቂዎቹ ገብተው ስማቸው ተመዝግቦ ዝምድናቸው ተጠይቆ «ለምን ትጠይቀዋለህ?» እያሉና እያስፈራሩ የነበረ ሲሆን የሚጠይቁት ኢትዮጵያውያን ግን ያለአንዳች ፍርሀት እየተመላለሱ የጠየቁት መሆኑን የገለፀው የእስር ቤት ምንጮች ጥቆማ የወያኔ ፖሊሶች ግን በንዴት ሲቃጠሉ እንደነበረም አስረድቷል::

ቴዲ አፍሮ እስር ቤት ከገባ በኋላ በጥቁር ካኔተራ ላይ «ጊዜ ለኩሉ» ብሎ ካሴቱ ላይ ያሳተመውን ፖስት ካርድ አድናቂዎቹ ካኔተራው ላይ አሳትመው በከተማውና በፍ/ቤት ግቢ ውስጥ ሲሸጡ የነበረ ሲሆን ይህም ያናደዳቸው ወያኔዎች ካኔቴራው እንዳይሸጥ መከልከላቸውም ታውቋል::

<u>**የሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ውሎ**</u>

ሰኞ ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ፍ/ቤት ቀርቦ የቅንጅት አመራሮችን ሲዳኝ የነበረው የሕወሓቱ ዋነኛ ካድሬ ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም በመሀል ዳኛነት ተሰይሞ የነበረ መሆኑን የዕለቱን ችሎት የተከታተሉት ምንጮች ግራና ቀኝ ያሉት ዳኞች አንቀፁ ይቀየር ሲሉ ልዑል የተባለው ሰው በላ ዳኛ ግን አይቀየር ብሎ ቢወስንም በድምፅ ብልጫ በማሸነፋቸው አንቀፁ አቃቤ ሕግ አሻሽሎ እንዲያቀርብ በሚል ትዕዛዝ ተሰጥቶት ረቡዕ ሚያዝያ 15 ቀን ተቀጥሯል::

*__የሚያዝያ 15 ቀን ውሎ__*

*ረቡዕ ሚያዝያ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ፍርድ ቤት በቀጠሮ የቀረበው ቴዲ አፍሮ ገና ከጠዋቱ 2 ሰዓት ሲል በትንሽ ነጭ መኪና ሕዝቡ እንዳያየው በአራት ፖሊሶች ተከብቦ ነበር የደረሰው:: ሕዝቡ ደግሞ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ወደ ፍ/ቤት ግቢ ለመግባት ተሰልፎ የነበረ ሲሆን ከሕዝቡ መብዛት የተነሳ ሰልፉ በሁለት ረድፍ ሆኖ ወደ ልደታ መስመር በረዥሙ እንደነበር የታየ እንደነበርና ሕዝቡ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወደ ፍ/ቤት ግቢ ለመግባት ሙከራ ያደረገ ቢሆንም እንደታሰበው ሳይሳካ ቀርቷል::*

*ይሁን እንጂ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሕዝብ ፍ/ቤት ግቢ ገብቶ ጉዳዩን ለመከታተል የቻለ ቢሆንም ችሎት ውስጥ ገብቶ ለመቀመጥ ግን እድል ተነፍጎ እንደነበር ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ምንጮች ገልፀዋል::*

*በእለቱ ስምንተኛ ችሎት ወትሮ ከሚሰየምበት ቦታ ቀይሮ የደርግ ባለስልጣናት የቀይ ሽብር ባለሥልጣናት ጉዳያቸው ሲታይበት በነበረው አዳራሽ የታየ ሲሆን ችሎቱን የሞሉት የወያኔ ደህንነቶችና የእስር ቤቱ ሹማምንቶች ብቻ እንደነበሩ ምንጮቹ አስረድተዋል::*

*ቴዲ አፍሮ ለሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጠው ሲሆን ይህንኑ የሰሙ በግቢው ውስጥ ያሉ አድናቂዎቹ እያለቀሱና እየጮሁ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰሙ ሲሆን በግቢው ውስጥ ያሉትን ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች አንድ ላይ በመሆን «ቴዲ ይፈታ፣ ቴዲ ይፈታ» እያሉ በከፍተኛ ድምፅ እያስተጋቡ ተቃውሟቸውን ሲገልፁ ታይተዋል::*

*በዚህን ጊዜ ፖሊስ የሕዝቡን ተቃውሞ ለማስቆም ሙከራ ያደረገ ቢሆንም የሕዝቡ ስሜት ገንፍሎ በመውጣቱና ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ሊቆጣጠረ ባለመቻሉ ተቃውሞው እየተስፋፋ ከግቢ ውጪ እንደቀጠለ ታውቋል::*

*በ10 ሺህ የሚቆጠር ሕዝበ ያቀጣጠለው ተቃውሞ ከከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ሜክሲኮ ድረስ በሶስት ምድብ ተከፍሎ የወያኔን ቡድን እያወገዘ ቴዲን እያሞገሰ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰማ ሲሆን ይህ የሕዝብ ቁጣ ያስደነገጣቸው ወያኔዎችበመቶዎች የሚቆጠሩ መከላከያ ያጠለቁና መሳሪያ የታጠቁ ፖሊሶችን አሰማርቶ ተቃውሞ ሰልፉ እንዲበተን ከማድረጉም በላይ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆኑ ሰዎች እየታፈሱ ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸው ታውቋል::*

*ቴዲ አፍሮ ዋስትና ለሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የተቀጠረ ሲሆን በእለቱ ምናልባትም ሕዝቡን ፈርተው የፍርድ ቤት ለውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ በብዙዎች ዘንድ ጠጣር ግምት ተሰጥቶታል::*

*ግራ የተጋባው ወያኔ በቅርቡ ደግሞ በራሱ ሚኒስትሮች ላይ ሹም ሽር እያደረገ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::*

ከውስጥና ከውጭ ከፍተኛ ተቃውሞ የገጠመው ወያኔ ግራ ከመጋባቱ የተነሳ የሚያደርገውን አጥቶ አንደ አበደ ውሻ እየተቅበዘበዘ አንዴ ሽቅብ ሌላ ጊዜ ቁልቁል እየተሯሯጠ በዚህ መሀል የራሴ ናቸው በሚላቸው ላይ እንኩዋን ሳይቀር እርምጃ እየወሰደ መምጣቱ ስርዓቱ አደጋ ውስጥ መግባቱን አመላካች ነው ሲልም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

በዚህም መሠረት ሰሞኑን ያገለግሉኛል፣ እመካባቸዋለሁ በተለይም ደግሞ እኔ ያልኩትን ሁሉ እንደ በቀቀን እያስተጋቡ እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ ረግጠው ይገዙልኛል በማለት በሙሉ አንደበቱ ሞልቶ ሲናገርላቸው ከነበሩት መካከል ዶ/ር ካሱ ኢላላን ከስልጣኑ ማንሳቱ ታውቋል።

ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እንደገለፁት ከሆነ ዶ/ር ካሱ ኢላላ የከተማ ልማት ሚኒስትር ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም ከሶስት ወር ወዲህ ግን ከመድረክም ጠፍቶ መስሪያ ቤቱን እንኩዋን በተመለከተ መግለጫ የሚሰጠው ምክትል ሚኒስትሩ የሐወሓቱ ሰው አርከበ እቁባይ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ ከሚኒስትርነቱ ቦታ አንስተውት ያንሳፈፉት መሆኑን የገለፁት እነዚሁ ወገኖች በምትኩ በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የነበረው ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደተሾመ አጋልጠዋል።

ሁለቱም የወያኔ ተላላኪዎች የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ብሎ ወያኔ የፈጠረው ቡድን አባላት ሲሆኑ ካሱ ኢላላ የጉራጌ ብሔር ተወላጅ ሲሆን፣ ኃይለማርያም ደሳለኝ ደግሞ ከአዋሣ የመጣ መሆኑን ጨምረው አስረድተዋል።

ወያኔ ሕዝቡ እጅግ ፊት እንደነሳው በተለይም በቅርቡ በሚያዝያ 5 ቀን እና በሚያዝያ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በትክክል ያረጋገጠ ሲሆን የሚያደርገው ሲያጣ በየማደያው እራሱ ቦምብ አፈንድቶ ንፁሃን ዜጐችን ገድሎ በርካቶችን ካቆሰለ በኋላ እንደለመደው ተልካሻ ድራማ ሰርቶ የሕዝቡን አንጀት ለማረጋጋት ሙከራ ያደረገ ቢሆንም ሕዝቡ ቀድሞት በመሄዱ ግራ ተጋብቶ መልሶ የራሱን ካድሬዎችም ግራ አጋብቷቸው ተቸግረው እንዳለ የነካሱ ኢላላ ማረጋገጫ ሊሆን እንደሚችል እነዚሁ ለጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀው በተለይም ኃ/ማርያም ደሳለኝ የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት በነበረበት በ1996 ዓ.ም የሲዳማ ብሔር ተወላጆች የዘንባባ ዝንጣፊ እና የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዘው ሠላማዊ ሠልፍ እናደርጋለን ባሉ ሎቄ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በርካታ ንፁሃን ዜጐችን በመትረየስ እንዲገደሉ ትዕዛዝ የሰጠ ቀንደኛ የወያኔ ካድሬ ሲሆን በሰራው ወንጀል መጠየቅ ሲገባው መለስ ዜናዊ ወደ ራሱ ቢሮ አስመጥቶ በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ አድርጐ የሾመው ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ምን ታመጣላችሁ በሚል የሲዳማን ሕዝብ በመናቅ ጉራጌውን ካሱ ኢላላን አንስቶ የከተማ ልማት ሚኒስትር

አድርጕ መሾሙ በጣም ልብ ድፍን መሆኑን የሚያሳይ ነው ሲሉ ቅርበት ያላቸው ወገኖች በቁጭት ይናገራሉ::

እንደነዚህ ወገኖች ገለፃ ከሆነ ዛሬ የካሱ ኢላላን መነሳትና ኃይለማሪያም ደሳለኝ መሾምን አወቅን እንጂ በዚህ አካሄድ ወደፊት በርካታ ሚኒስትሮች የካሱ ዕጣ ፈንታ እንደሚደርሳቸው እንገምታለን ሲሉ ገልፀዋል::

ከወራቶች በፊት መለስ ፊት የነሳውንና ያለ ስራ ያስቀመጠውን በረከት ስምኦንን ከሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የቀድሞ ቃል አቀባይነቱን ስራ እንዲጀምር ማድረጉን እነዚሁ የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

የሚናገረውን የማያውቅ ኤርትራዊ ደም ያለበት አንደበቱ እሬትና ምንም የኢትዮጵያዊነት ባህል የማይገለፅበት ነው ተብሎ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚገለፀው ይኸው በረከት ስምኦን የተባለው ግለሰብ ለብዙ ዓመታት ከመለስ ዜናዊ ባልተናነሰ መልኩ ሐገሪቷንና ሕዝቧን እረደው፣ እጨደው፣ ዝረፈው እያለ ሕዝቡን ሲያስጨርስ የነበረ ግለሰብ ሲሆን በ1997 ዓ.ም የወያኔው ቡድን ለከፍተኛ ኪሣራ የዳረገው መሆኑን ሕወሓቶቹ በማወቃቸው ከነበረበት የማስታወቂያ ሚኒስትርነት አንስተው በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት አማካሪ ሆኖ የተቀመጠ ቢሆንም በቃለ አቀባይነት ሲያገለግል የቆየ ሲሆን ከወራቶች በፊት ግን በተለይ የታሰሩትን የቅንጅት አመራሮችን በተመለከተ በሰጠው መግለጫ መልሶ ወያኔን በመወንጀሉ ላልተወሰነ ጊዜ ከስልጣኑ ተነስቶ ጃሌ ሆኖ የቆየ ሲሆን በቅርቡ ወደ ቦታው እንዲመለስ የተወሰነለት መሆኑን ገልፀዋል::

በዚህም መሠረት እሱ በተነሳ ጊዜ የቃል አቀባይነቱን ስራ ሲሸፍን የነበረው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ገ/ዋህድ የተባለው የህወሓት ሰው የነበረ ሲሆን አሁን በረከት ወደ ቀድሞ ስራው በመመለሱ እንደለመደው የጭቃ ጅራፉን እያወናጨፈ መሆኑን ሰሞኑን ከሰጠው መግለጫ ለማወቅ ተችሏል::

እድሜና ትምህርት ያልለወጠው ይኸው በረከት ስምኦን የተባለው ግለሰብ የተወለደበትን አካባቢ እንኳዋን ባለማወቅ በወሎ ውስጥ በላሊበላ ወረዳ እንዲወዳደር ተደርጕ በሰፊ ድምፅ የተሸነፈ ቢሆንም ጦር አዝምቶ በድጋሚ እንዲያሸንፍ ያደረገ ከመሆኑም በላይ በርካታ ሰዎች እንዲገደሉ ያደረገ አውሬ ነው ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች በቁጭት ሲገልፁ እንደነበረም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በአሁን ሰዓት እጅግ ግራ ተጋብቶ የሚያደርገው ያጣበት ወቅት ላይ ሲሆን፣ ለማስመሰልም ቢሆን «ስልጣኔን እለቃለሁ በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትር መባል ሰልችቶኛል» በማለት ለኒውስ ዊክ ለተባለው መፅሄት

የገለፀ ሲሆን፣ መለስ ጠ/ሚ/ር የሚለውን ስም መለወጥ ከፈለገ የሀገሪቷን ሕግ በ24 ሰዓት ሽሮ ሙሉ ስልጣኑን ለፕሬዝዳንቱ አዛውሮ ዳግም ፕሬዝዳንት ለመባል አስቦ ይሆናል ሲሉም አንዳንድ ምሁራኖች የመለስን ገለፃ ሲያጣጥሉ ተደምጠዋል።

ወያኔ እራሱ በመጣው ጣጣ መልሶ እራሱ እየተለበለበ በርካታ ወታደሮችን እያስፈጀ ሲሆን፣ በቅርቡም በአፋር ክልል በተከሰተ ችግር ምክንያት በርካታ የጦሩ አባላት ላይ ጉዳት እንደደረሰ የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ ምንጮች ገልፀዋል።

በገዋኔ፣ በዲቼኦቶ፣ በገደማይቱና በተለያዩ የአፋር ክልል በረሀዎች ውስጥ ታጣቂዎች በሚሰነዝሩት ድንገተኛ ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ያሉት የወያኔ ወታደሮች በሁኔታው በመማረራቸው የተነሳ ወደ አዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ተወስደው የነበረ ሲሆን በምትካቸው የፌዴራል ፖሊስ አካባቢውን እንዲጠብቅ በሚል አንድ የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን የያዘ ቡድን ወደ አካባቢው ተጉዞ መመለሱን ምንጮች ገለፁ።

ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን 2000 ዓ.ም የተጓዘው ይኸው የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ ባለሥልጣናት ቡድን በርካታ ቁጥር ያለው የፌዴራል ፖሊስ ኃይልን ይዞ ሄዶ ሰመራ፣ አሳኢታ፣ ሎጊያ፣ ገዋኔ፣ ዱብቲ እና ሌሎችም ቦታዎች እንዲሰፍርና ሌላ ተጠባባቂ ጦር በአዋሽ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ እንዲቀመጥ አድርገው የተመለሱ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አስረድተዋል።

ቀድሞ ከየቦታው ተሰብስቦ በአዋሽ ወታደራዊ ማሰልጠኛ የነበረው ሠራዊት ወዳልታወቀ ስፍራ የተወሰደ ሲሆን በምትኩ ተወርዋሪው የፌዴራል ፖሊስ ሰፍሮ የሚገኝ መሆኑን የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ከጅቡቲ ወደ መሀል ሀገር የሚንቀሳቀሱ መኪኖችም ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት በጭንቀትና በፍርሃት መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በጐንደር እና በኦጋዴን እንዲሁም በሌሎችም አካባቢዎች በወታደራዊ ውጥረት ውስጥ የገቡ ሲሆን በተለይ በሰሜን ጐንደር እና በኦጋዴን ያለው ውጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደሆነ የመከላከያ ምንጮች አጋልጠዋል።

ለኦጋዴን ጦር አጋዥ ይሆናሉ ተብለው የተመደቡ የጦር ሂልኮፕተሮች በጅጅጋ የተቀመጡ ሲሆን፣ ለጐንደር ላለው ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይል መምቻ ተብሎ ደግሞ ተዋጊ ጀቶችና የጦር ሂልኮፕተሮች በባህርዳር እንደተዘጋጁ ምንጮች ገልፀው በአሁን ሰዓት በወያኔ ወታደራዊ ተቋም ውስጥ ያለው የአንድ ብሔር የበላይነት ችግር የአባላቱን ሞራል ያደቀቀ በመሆኑ ሁሉም ቀዳዳና አጋጣሚ የሚጠብቅ እንደሆነ ምንጮቹ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል በውያኔ የፓርላማ ጽ/ቤት ቋሚ ሠራተኞች ሰሞኑን ባደረጉት የውስጥ ግምገማ አርኪ አይደለም በማለት ተሾመ ቶጋ በግምገማው ላይ ለመሳተፍ

ጥረት ቢያደርግም ሠራተኛው አቋም ወስዶ «ይህ ግምገማ ቋሚ ሠራተኞችን እንጂ የተመራጮችን አይመለከትም» በማለት አሳፍረው እንደመለሱት የም/ቤቱ ምንጮች አጋለጡ፡፡

ለሁለት ቀናት በተካሄደው ግምገማ ላይ ሠራተኛውን እርስ በእርሱ እንዲሰዳደብና በጥላቻ ቀለበት ውስጥ ገብቶ አንዱ አንዱን እንዲያጋልጥ ታስቦ የነበረ ቢሆንም ወያኔዎች እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ሁሉም በጨዋነት በተላበሰ መልኩ በማሳለፉ የተናደደው ተሾመ ቶጋ በግምገማው ማጠቃለያ ላይ እገኛለሁ በማለት ወደ አራዳሽ ቢገባም ሠራተኛው አይመለከትህም በማለት እንዳባረረው ይኸው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፃ ያስረዳል፡፡

ይህንኑ ተከትሎ ከወራት በፊት የተጀመረው የሠራተኛ አዲስ መዋቅር ምደባ በርካቶችን ከስራ ለማባረር ያቀደና ለዚህም ሆን ተብሎ የተሠራው ስራ ጥናቱ ተጠናቅቆ ወደ ተግባር በቅርብ ቀን ይለወጣል እየተባለ እንደሚገኝም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት በዚሁ መ/ቤት ውስጥ ሲያገለግሉ የቆዩት በርካታ ሠራተኞች በወያኔ ካድሬዎች ዘንድ የአይናችሁ ቀለም አላማረንም ብለው ሊባረሩ እንደሚችል ስጋት ስላደረባቸው በየቀኑ ለስራ እንኳዋን ሲጠሩ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ገብተው እንዳሉ ምንጮች ጠቁመው ይህንን ማስፈራሪያ እያደረገ ተሾመ ቶጋ እየተጠቀመበት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ቡድን መላው የሀገሪቱን ህዝቦች በችግርና በመከራ ውስጥ ዘፍቆ አግር ከወርች አስሮ አንደበቱን በመሣሪያ ኃይል ሸብቦ እንዳይናገር ከማድረጉም በተጨማሪ የመንግስት ሠራተኞችን በመዋቅር ለውጥ በሚል ሰበብ ከስራቸው ሊያፈናቅላቸው መዘጋጀቱን ለሲፒኤ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ፡፡

እንደነዚሁ ወገኖች ገለፃ ቢ.ፒ.አር አዲስ የመዋቅር ጥናት ተደርጓል በሚል በቅርቡ ተግባራዊ የሚሆን፣ በርካታ ሠራተኞችን ለዘመናት ከሰሩበት መ/ቤት የሚያፈናቅል ሲሆን፣ በምትኩ የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎችን እያመጡ ለመሰግሰግ እቅድ እንደተያዘም አጋልጠዋል፡፡

የተወካዮች ም/ቤት ቋሚ ሠራተኞችም የዚሁ ሰለባ ሊሆኑ እንደሚችሉም ቀድመው በማወቃቸው በርካታ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ያሉበት በመሆኑ «ልጆቻችንን ምን እናደርጋቸዋለን?» በማለት በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንዳሉ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው በምትካቸው ከተለያዩ አካባቢ የመጡ የወያኔ ካድሬዎችን ሊያስገቡ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን አክለው ገልፀዋል፡፡

በአሁን ሰዓት በየትኛውም መንግስታዊ መስሪያ ቤት ውስጥ ሠራተኛ እንዳቀጠር እና እድገትም እንዳይሰጥ የሚል መመሪያ ማስተላለፋቸው ታውቋል፡፡

የወያኔ ቡድን ከአዲስ አበባና ከሌሎች የሀገሪቷ ክፍሎች ውስጥ አፍሶ የሚያመጣቸው ዜጐችን በቃሊቲ አስር ቤት እያጕራቸው ሲሆን በአሁን ሰዓት ከ8-10 ሺህ እስረኞች በዚሁ ግቢ እንደሚገኙ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ከውስጥና ከውጭ የፖለቲካ ጫና ስለበዛበት ሕዝቡን እያፈሰ እስር ቤት እያጋዘ ሲሆን በአዲስ አበባ ውስጥ አፈሳው ቀጥሏል፡፡ በዚህም የተነሳ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ለወያኔ ገንዘብ አውጡ ተብለው አናዋጣም ያሉትን በስም ዝርዝር እየለቀሙ ለእስር እየዳረጓቸው ሲሆን፣ ጥቂቶቹ በማዕከላዊ ምርመራ ሲገኙ የተቀሩት ለጊዜው የት እንደታሰሩ እንኳዋን ቤተሰቦቻቸው ባለማወቃቸው ተቸግረው እንዳሉም ለታሣሪ ቤተሰቦች ቅርበት ያላቸው ወገኖች አጋልጠዋል፡፡

የቃሊቲ እስር ቤት በእስረኞች በመጨናነቁ የተነሳ ቅዳሜ ሚያዝያ 11 ቀን 2000 ዓ.ም 6 አውቶቡስ ወደ ዝዋይ የወሰደ ሲሆን 2 አውቶቡስ ደግሞ ወደ ሸዋሮቢት እስረኞችን ያጓጓዛቸው መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው አሁንም በተከታታይ እንቅስቃሴው እንደሚቀጥል ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ለወያኔ ስርዓት ከፍተኛ አገልጋይ ናቸው ተብለው በከፍተኛ የስልጣን ቦታ ተቀምጠው የነበሩ ከበረሀ የመጡ ፖሊሶች አሁን የተሰጣቸውን ኃላፊነት በዚያው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የመኮንነት ኮርስ እንዲገቡ መደረጉን ታወቀ ፡፡

ኪዚህ ቀደም በአሌልቱ ፖሊስ ማሰልጠኛነት የሚታወቀው ይኸው ካምፕ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ነገር ግን ለወያኔ ካላቸው ቅርበት ብቻ ኮርስ ግቡ ተብሎ በ9 ወራት ውስጥ አስመርቆ በመኮንነት ሊያንበሻብሻቸው መሆኑን የገለፁት ምንጮች ሌላ ቀጣይ ተከታዮችም እንደሚኖሩ ገልፀው በትምህርታቸው የተሻለና ዲፕሎማ ያላቸው ፖሊሶች ቢኖሩም ይህኛው እናንተን አይመለከታችሁም ተብለው ከኮርሱ እንደተከለከሉና በጥበቃ ሠራተኞችና አስተዳደሮች መካከል ኩርፊያ መጀመሩን ምንጮች ለ ጨምረው ገልፀዋል፡፡